# ዘወርዋራው የቀለም አብዮት መንገድ

**አለባቸው ፍቃዱ**

**ትግራይ ኦንላይን April 12, 2014**

የቀለም አብዮት የሚለው ቃል በስፋት አገልግሎት ላይ መዋል የጀመረው በፈረንጆቹ አቆጣጠር ከ2000 ጀምሮ ነው፡፡ ሥያሜውንም በስፋት የሚጠቀሙት የምዕራብ ሚዲያዎች እንደሆኑ አንዳንድ ማስረጃዎች ያሳያሉ። የቀለም አብዮት በአብዛኛው ከታየባቸው አካባቢዎች በዋነኝነት የሚነሱት የቀድሞዋ የሶቭየት ህብረት አባል በሆኑ አገራትና በምሥራቅ አውሮፓ በተለይ ባልካን በመባል በሚታወቁት አገራት ቀጠናዎች ነው።

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃተ በኋላ የምዕራባዊያን የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት የሆነው በምህጻረ ቃል ኔቶ በመባል የሚታወቀው፣ በምሥራቅ አውሮፓ መስፋፋት እንዲችልና ሩሲያ በአካባቢው የነበራትን የበላይነት ለማዳከም ሲሉ  በቀጠናው ያሉ በህዝብ የተመረጡ መሪዎችን  በቀለም አብዮት  በተቀነባበረ ሴራ ከሥልጣናቸው እንዲወገዱ  ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

እስካሁን የተሳኩም ይሁኑ የከሸፉ ብቻ የቀለም አብዮት ሙከራዎች የተካሄደባቸው አገሮች በርካቶች ናቸው። እነዚህ የቀለም አብዮቶች አብዛኛዎቹ የተለያዩ የቀለሞችና አበቦች መጠሪያ ሥያሜዎች ተሰጥቷቸዋል። ከእነዚህም መካከል  ዋና ዋናዎቹ  እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2000  በሰርቢያ የተካሄደው አብዮት **ቡልዶዘር** አብዮት  ሲባል፣ በ2003 ላይ በጆርጂያ የተካሄደው **ጽጌረዳ** (ሮስ) አብዮት፣ በዩክሬን በ2004 ደግሞ ብርቱካናማ ወይም (ኦሬንጅ) አብዮት የሚሉ ናቸው፡፡

በኪርጊስታን በ2005 **ቱሊፕ** አብዮት**፣** በሚያዝያ 2005 በሊባኖስ ከራፊቅ ሀሪሪ ግድያ ጋር በመያያዝ የተነሳው **የሴዳር አብዮት**፣ **የፐርፐል** አብዮት በኢራቅ (ይህ አብዮት ይህን ስያሜ ያገኘው በወቅቱ የአሜሪካ መሪ ከነበሩት ጆርጅ ደብሊው ቡሽ ነው) ግጭቱ የተነሳው የ2005 የአገሪቱ ምክር ቤት ምርጫን ተከትሎ ነበር **አረንጓዴው** አብዮት፣ የ2009ኙን የኢራን

ፕሬዚዳንታዊ ምርጫን ተከትሎ የተነሳው አመፅ፣ በ2007 በበርማ **ሳፋሮን** አብዮት፣ በአርሜንያ  2005፣ አዘርባጃን 2005፣ ቤላሩስ በ2005ና 2006፣ ሞልዶቫ 2005፣ ሞንጎሊያ 2005፣ እንዲሁም በኡስቤኪስታን፣ ኪርግስታን፣ በቻይና ቲቤት “የክሪምሰን አብዮት” የነበሩት ተጠቃሽ የቀለም አብዮቶች ናቸው።

የቀለም አብዮት በአብዛኛው ምርጫን ተከትሎ የሚደረግ አመጽ ነው፡፡ ድምፃችን ተጭበርብሯል፣ የምርጫው ሂደት ትክክል አይደለም  ወዘተ በሚል ሽፋን ይቀስቀስ እንጂ፣ አንዳንዴ ከምርጫ  ውጪ

በሆነ ወቅትም የሚደረግ ነውጥ ነው። የቀለም አብዮተኞች በውክልና ወይም በሦስተኛ አካል ፍላጎት በጎዳና ላይ ነውጥ በህዝብ ድምፅ ሥልጣን የያዙ መንግሥታትን ከሥልጣን የማውረድ ሙከራ ወይም ሴራ ነው።

የቀለም አብዮት ሙከራዎች ስኬት ያገኘባቸው ወይም የከሸፈባቸውን አገራትን ሁኔታ ስንመለከታቸው በአብዛኛው የምዕራባዊያን እጆች እንዳሉባቸው የሚያሳዩ ነገሮችን ማስተዋል ይቻላል። ለዚህም ነው ብዙዎች የቀለም አብዮትን በውክልና ወይም በሦስተኛ አካል ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የሚካሄድ መፈንቅል በማለት የሚጠሩት። በምዕራባዊያን የገንዘብ እገዛ የሚደረጉ አንዳንድ የተራድኦና የልማት ድርጅቶች በታዳጊ አገራት ቀለም አብዮቶች ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳላቸው የራሳቸው የምዕራባዊያን ንብረት የሆኑ ትላልቅ ሚዲያዎች ያረጋገጡት እውነታ ነው።

**ዘጋርዲያን፣ ዋሽንግተን ፖስትና ኒዮርክ ታይምስ** ያሉ ሚዲያዎች በልማት ተራድኦ ድርጅቶቻቸው ስም ምዕራባዊያኖች እጆቻቸውን በታዳጊ አገራት በሚካሄዱ የቀለም አብዮቶች ውስጥ እንደሚከቱ በግልጽ ምስክርነታቸውን አስቀምጠዋል።

እነ ዩ ኤስ ኤይድ፣ ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ፣ ኢንተርናሽናል ሪፑብሊካን ኢንስቲትዩት፣ ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ፎር ኢንተርናሽናል አፊርስ፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ ፍሪደም ሃውስ፣ አልበርት ኢንስታይን ኢንስቲቱዩት፣ ኢንተርናሽናል ክራይስ ግሩፐ የመሳሰሉ ትላልቅ የልማት ድርጅቶች በተለያዩ አገራት የተካሄዱ የቀለም አብዮቶችን በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር በማስተባበርና በመምራት ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳላቸው እነዚህ ሚዲያዎች ዘግበዋል።

ሩቅ ሳነሄድ በእኛ አገር በ1997ቱ የምርጫ ሂደት ወቅት **አቶ ዳንኤል በቀለ** ይመሩት በነበረው የልማት ድርጅት (ለጊዜው ስሙ ይቆይልኝ) ከቅንጅት አባላት እንደ አንዱ በመሆን ሲንቀሳቀሱ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ህዝብና መንግሥት የእነ አቶ ዳንኤልን ድብቅ አጀንዳ በጊዜው ስለነቃበትና መቆጣጠር በመቻሉ በአገራችን ይከሰት የነበረውን ቀውስ መቆጣጠር ተቻለ እንጂ የሚያስከትለው መዘዝ በቀላሉ የሚታለፍ አልነበረም።

እነሂዩማን ራይትስ ዎች፣ ኢንተርናሽናል ክራይስ ግሩፕ፣ ሲፒጄ፣ ሰርቫይቫል ኢንተርናሽናል የመሳሰሉት ድርጅቶች ተጨባጭነት የሌላቸው ክሶችን በማያቋርጥ ሁኔታ በመንግሥት ላይ ሲደረድሩ ይታያሉ። ጆሮጅ ሶሮስ የተሰኘው ቢሊዮነር በአለም ላይ የታወቀ የቀለም አብዮት አባት ሲሆን "ሁሉንም ነገር ለገበያውና ለባለሀብቱ መተው አለበት፤መንግስት ህግና ስርዓትን ከማስከበር ባለፈ ኢኮኖሚው ውሰጥ እጁን ማስገባት የለበትም" በሚል የገበያ አክራሪነ መርህ የኒዮ ሊበራል አይዲዎሎጂን ለማስጠበቅ በአለም ላይ ያሉ አገራትን በሙሉ በማስገደድም ቢሆን የዚህ አይዲዎሎጂ ተከታይ እንዲሆኑ ለማድረግ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ግዙፍ ሃብቱን በማፍሰስ የሚንቀሳቀስ አምባገነን ነው ።

የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ  ድርጅት ነኝ ባዩ ሂዩማን ራይትስ ዎች ሰብዓዊ መብትን ለማስጠበቅ የቆመ ድርጅት ሳይሆን ሥውር የፖለቲካ ተልዕኮ ለማሳከት  በግልጽ የሚንቀሳቀስ ድርጅት መሆኑን አገራችንን አስመልክቶ በተከታታይ የሚያወጣቸውን ውንጀላዎች መመልከቱ በቂ ይሆናል። በኢትዮጵያ ከጋዜጠኝነት ሥራው ጋር በተያያዘ ማረሚያ ቤት የገባ አንድም ጋዜጠኛ እንደሌለ እየታወቀ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ነን ባዩ ድርጅት በየጊዜው የሚያወጣቸው ሪፖርቶች ላይ እንደ ቅመም በኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ታስረዋል የሚል ውንጀላ ሳያቀርብ ያለፈበት አንድም ወቅት የለም።

በተመሳሳይ ሂዩማን ራይትስ ዎች  መንግሥት  በኃይማኖት ጣልቃ እንደገባ በማድረግ  የተለያዩ ውንጀላዎች ሲያቀርብ ቆይቷል። ሂዩማን ራይትስ ዎች  ሰሚ ጆሮ ሳያገኝ ቀረ እንጂ ህዝቡ በመንግሥት ላይ  አመጽ እንዲያስነሳና አገሪቱ እንድትበጠበጥ ባለው ፍላጎት ብዙ ደክሟል፡፡

እስካሁን የቀለም አብዮት ሙከራ የተደረገባቸው መንግሥታት ሁኔታዎች ስንመለከታቸው የምዕራባዊያን ልዩ ፍላጎት የሚያሳድሩባቸው አገሮች ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሥሌ፣ በምስራቅ አውሮፓ የተደረጉት የቀለም አብዮት ሙከራዎች በአካባቢው ያለውን የራሽያን የበላይነት ለማዳከምና ኔቶን ለማስፋፋት ነው፡፡ በሌሎች አገሮች የተደረጉት የቀለም አብዮት መከራዎች ደግሞ  የምዕራቡን የኒዮ-ሊበራሊዝም  የገበያ ፍልስፍናቸውን በማስፋፋት የአገሮቻቸውን ባለሃብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ሲሉ ነው። የምዕራባዊያንን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፍልስፍና  አምኖ መቀበል አሊያም እንደ ቻይናና ሩሲያ ራስን በቴክኖሎጂውና በኢኮኖሚው ማጠንከር ካልታቻለ በስተቀር  ከቀለም አብዮት ሙከራዎች ማምለጥ አስቸጋሪ ነው። በምዕራባዊያን መሥፈርቶች መሠረት የታዳጊ አገር መሪዎች አገሩን የመምራት ወይም ማስተዳደር ያልቻለ የአገር መሪ፣ አምባገነን የሚል ታርጋ ይለጠፍለትና የተለያዩ ውንጀላዎች ይፈበረኩለታል።

የዚምባቡዌ መሪ ሮበርት ሙጋቤ አምባገነን ሊባሉ የሚችሉ መሪ ቢሆኑም፣   በምዕራባዊያን ሚዲያዎች ጭራቅ ተደርገው እንዲታዩ ቀን ከሌት ይሰራ የነበረው ሥራ የአገሪቱን ለም መሬት  ጠቅልለው ከያዙ ጥቂት ነጮች መሬት በመንጠቅ ለተገፉ ደሃ ጥቁር ገበሬዎች በማከፋፈለቸው ነው። ምክንያቱም ሮበርት ሙጋቤ ይህን ለጥቁር ገበሬዎች መሬት ከማከፋፈላቸው በፊት በአንድም የምዕራብ አገር አምባገነን ናቸው ተብለው የማጥላላት ዘመቻ ተከፍቶባቸው አልሰማንም።

ላለፉት ሰላሳ አመታት ፈጣንና ተከታታይ የሚባል የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግበዋል። በዚህም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ ባቀዱት ጊዜ ውስጥ ለመቀላቀል በቅተዋል። ይህም በአሁኑ ወቅት በተለይም ቻይና ኢኮኖሚዋ በከፍተኛነቱ ከሚታወቀው የአሜሪካ ኢኮኖሚ ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆን አስችሏታል።ይሁን እንጂ ቻይና ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ባስመዘገበችባቸው ያለፉት ሰላሳ አመታት ጉዞ እንዲሁ አልጋ በአልጋ አልነበረም፤ በእነዚህ አመታት ሂዩማን ራይትስ ዎችና መሰል ፅንፈኛ የአክራሪው የኒዮ

ሊበራል ሃይል ጋር በመተባበር  የሃሰት ሪፖርትና መግለጫ በዴሞክራሲና በሰብዓዊ መብት ሽፋን የዘመቻ ናዳ ሲያውርድባት እንደነበር የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ሆኖም ግን የቻይና መንግስት ይህን መሰል ጫናዎችንና ዘመቻዎችን በመቋቋም ከቀየሰው የልማት መስመር ሳያፈንግጥ የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ግስጋሴ በአለም ግዙፍ ከሚባሉት ኢኮኖሚዎች ተርታ እንዲሰለፍ አስችሎታል።ሂዩማን ራይትስ ዎች ምንም እንኳን ተሳክቶለት ውጤታማ መሆን ባይችልም ቀደም ሲል በተጠቀሰው መልኩ ለረዥም ዘመናት የሀሰት ዘመቻ ከከፈተባቸው የኤስያ አናብስትና ቻይና በተጨማሪ የቀለም አብዮት እስከ መቀስቀስ የሚዘልቀው የዚሁ ዘመቻው ሰለባ በመሆን ደግሞ ዩክሬንና ጆሪጂያንን ይጠቀሳሉ ።

እ.ኤ.አ. በ2007 ኸርማን ፣ ፒተርሰን እና ዛሙሊ የተባሉ ፀሐፍት ሂዩማን ራይትስ ዎችን አስመልክቶ ባሳተሙት ጥናት ድርጅቱ በሰብዓዊ መብት ሽፋን በዩጎዝላቪያ ባካሄደው ጣልቃ ገብነት  አገሪቱን ለመበታተን ያበቃትን አሉታዊ አስተዋፅኦ ማበርከቱን አስረግጠው ገልፀዋል።

ምሁራኑ በዚሁ ጥናታቸው ሂዩማን ራይትስ ዎች በዩጎዝላቢያ “ለሰብዓዊ መብት መጠበቅ ቆሜያለሁ” የሚለው ይሀው ተቋም በአገሪቱ የተቀሰቀሰውን የእርስ በእርስ ግጭት እንደ ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም እ.ኤ.አ. ከ1992 ጀምሮ ሰብዓዊ መብቶች የሚዳከሙበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት እንዲሁም በወቅቱ የሰሜን ቃል ኪዳን አባል ሀገራት ጦር (ኔቶ) በአገሪቱ ላይ የፈፀመውንና “ከፍተኛ ዓለም አቀፍ ወንጀል” የሚባለውን ተግባር እንዲያከናውን መደላድል ፈጥሯል።

በአገራችንም አንዳንድ ሁኔታዎች ስንመለከት የኢትዮጵያ  መንግሥት የሚከተለው  አብዮታዊ ዴሞክራሲ አካሄድ አንዳንድ የምዕራብ  አገራትን አያስደስታቸውም። የኢትዮጵያ  መንግሥት  የሚከተለው ልማታዊ ዴሞክራሲ አካሄድ  የኒዮ ሊበራል ትርፍ ማጋበሻ የሆኑ ተቋማት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መቆየታቸው የምዕራብ መንግሥታትን አያስደስታቸውም።

ለዚህም የምዕራባዊያን ኩባንያዎች በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ትላልቅ ተቋማትን እንዲቆጣጠሯቸው ለማድረግ እንዲችሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ሁሉንም ነገር ለግል ባለሃብት መስጠት አለባት የሚል መከራከሪያ ያነሳሉ።  መንግሥት የባንክ አገልግሎትን ለውጭ ባለሃብቶች ክፍት ማድረግ አለበት፣ መሬት የግል ንብረት መሆን መቻል አለበት፣ ቴሌኮሙዩኒኬሽንና መብራት የመሳሰሉት ተቋማት ከመንግሥት እጅ በመውጣት በግል ባለሃብት መተዳደር አለበት በሚል ስም መንግሥት ላይ ከፍተኛ ጫና በመፍጠር ላይ ይገኛሉ።

መንግሥት ላይ ጫና በመፍጠር እነዚህን የልማት ተቋማት ወደ ግል በማዞር ኩባንያዎቻቸውን ከመጥቀም በዘለለ በፈለጉ ጊዜ እነዚህን ኩባንያዎቻቸውን በመጠቀም የመንግሥትን እጅ ለመጠምዘዝ እንዲያስችላቸው ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል።

ይህ የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ነኝ ባይ ድርጅት ያሰበው ነገር አልሳካ አለው እንጂ ኢትዮጵያን በሚመለከት ከውንጀላ የቦዘነበት አንዳችም ጊዜ የለም። ለአብነት ያህል ጋዜጠኞች ታሰሩ፣ ዜጎች በኃይል ተፈናቀሉ፣ መንግሥት በኃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ገባ፣ በማረሚያ ቤት ያሉ ሰዎች በአግባብ አልተያዙም፣ አሁን በቅርቡ ደግሞ መንግሥት ስልክ በመጥለፍ የግለሰቦችን ሚስጥር ይመረምራል በማለት እጅግ ከእውነት የራቁ ውንጀላዎችን ሲደረድር ቆይቷል። ነገ ደግሞ ምን ዓይነት ውንጀላ ያቀርብ ይሆን? ምዕራባዊያን በሚዲያዎቻቸው **የቀለም አብዮትን** የአምባገነን መሪዎችን ከሥልጣን ማስወገጃ ከአመጽ የራቀ (non violent) የህዝብ መአበል በማለት ሲያንቆለጳጵሱት ይደመጣሉ። ነገር ግን ጦሱ የሚተርፈው ለአገሪቱና ለህዝቡ ነው። "በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት" እንደሚባለው ዛሬ ሶሪያዊያኖች ሁኔታ የተመለከተ የሦስተኛ አካል ጣልቃ ገብነት ምን እንደሆነ ጥሩ አስረጅ ይሆናል።

በምዕራባዊያኖች ስለ ሰብዓና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ተብለው የተቀመጡ መሥፈርቶች ወጥነት የሚጎድላቸው የራሳቸውን ጥቅም ማስጠበቂያ እንጂ እውነትም ለሌሎች ህዝቦች ነጻነት ሲባል ያለመሆኑን ማየት ይቻላል።

ለአብነት ያክል ሂዩማን ራይትስ ዎች በኢትዮጵያ መንግሥትን በጋምቤላ አካባቢ ያሉ ነባር ዜጎችን በኃይል በማፈናቀል አካባቢውን ለውጭ ኢንቨስተሮች በመስጠት ላይ ነው የሚል ውንጀላ ያቀርባል። የዚህን ውንጀላ ጉዳይ እስቲ እንመልከተው። በዚህ አካባቢ ያሉ ዜጎቻችን አርብቶ አደሮች በመሆናቸው ከሌላው የአገራችን ክፍሎች በባሰ ሁኔታ ምንም ዓይነት የመሠረተ ልማት አቅርቦት ያልተዳረሰበት አካባቢ ነው።

የትምህርት፣ የጤና፣ የመንገድ፣ የመብራት፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ከህብረተሰቡ ጋር ምክክር በማድረግ በተቻለ አቅም በሰፈራ ማሰባሰብ አስፈላጊቱ ታምኖበታል። መንግሥት ከህብረተሰቡ ጋር በመመካከር ዜጎች እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያገኙ ለማድረግ በሰፈራ የማሰባሰብ ሥራ ማከናወኑ ክፋቱ ምን ላይ ነው?

እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች መሠረታዊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን የማግኘት መብት የላቸውምን? በምዕራባዊያን ከተቀመጡ የዴሞክራሲያዊ መንግሥት አንዱ መሥፈርት በዜጎች መካከል ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል እንዲኖር ማስቻል አይደለምን? ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል የሚባለው ዜጎች በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች እኩል ተጠቃሚ መሆን ሲችሉ ብቻ ነው። ዜጎች መብትና ግዴታቸውን ሊያውቁ የሚችሉት የትምህርት እድል ተጠቃሚ ሲሆኑ ነው።

እንግዲህ ሂዩማን ራይትስ ዎች እውነት ለእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች በማሰብ ነው ወይስ የኢትዮጵያን መንግሥት ለማሳጣት ይሆነኛል በሚል የተሳሳተ መነሻ ባገኘው ነገር ውስጥ ሲንቦጫረቅ የሚስተዋለው? ምዕራባዊያኖች በራሳቸው መሥፈርት አምባገነን የሚሏቸውን የአገር መሪዎች ለመገልበጥ

እንዲያመቻቸው የቀለም አብዮቶችን በተለያየ መንገድ ሲደግፏቸው ይስተዋላሉ። ከአብዛኛዎቹ የቀለም አብዮቶች ዙሪያ የምዕራባዊያን እጆች ይታያሉ።

ለቀለም አብዮት መነሻ ናቸው ተብለው በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ነገሮች መካከል መንግሥት ዴሞክራሲያዊ አይደለም፣ በሥልጣኑ ባልጓል፣ አምባገነን ሆኗል ወይም በሙስና ተዘፍቋል የሚሉ ነጥቦች ናቸው።

እነዚህን መነሻ በማድረግ  የቀለም አብዮት እንዲካሄድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ቀውስ እንዲነሳ ካደረጉ በኋላ ግጭቱን ወይም ብጥብጡን ሠላማዊ  ተቃውሞ  በማለት በማሞካሸት ሰፊ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ ያደርጉታል።

ለዚህ ጥሩ ማሣያ ማንሳት ይቻላል። በቅርቡ በዩክሬን የተካሄደው የቀለም አብዮት እያንዳንዷን ነገር የአየር ሽፋን እንዲያገኝ በማድረግ ለህብረተሰቡ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት አመፁ እነሱ በፈለጉት መንገድ እንዲሄድ አድርገውታል።

ይሁንና የመሩት መንገድ የዩክሬንን ሉዓላዊነት ከመጉዳቱም በላይ  የግዛቲቱ አካል የሆነችው ክሬሚያን እስከማሳጣት ደርሷል። ዛሬም ዩክሬናዊያኖች ከትናንቱ ስህተታቸው ካልተማሩ ሌሎች ግዛቶቻቸውም አብረዋቸው ስለመዝለቃቸው ምንም ማረጋገጫ ያላቸው አይመስልም። የቀለም አብዮት ወይም የውክልና አብዮት መጨረሻው ይህ ነው።

እዚህ ላይ ማንሳት የምፈልገው የቀለም አብዮት አያስፈልግም ማለቴ አይደለም። ነገር ግን አብዮቱ መካሄድ ያለበት በውክልና ሳይሆን በህዝቡ ፍላጎት መሆን ይኖርበታል። በዓለማችን ላይ እጅግ የከፉ አምባገነኖች በቀለም አብዮት መነሻነት ተፈንግለዋል። ለአብነት የዐረብ ፀደይ በመባል በሚታወቀው የዐረቡ አብዮት የቱንዚያው ቤን አሊ፣ የግብፅ  ሙባረክ፣ የሊቢያው ጋዳፊን ወዘተ ማንሳት ከሥልጣን መንበራቸው አሽቀንጥሮ እንደጣላቸው ማየት ይቻላል።

የአሜሪካ ጥብቅ ወዳጅ የሆነችው የሣውዲ ዐረቢያ መሪዎች ከሌሎች አምባገነን ተብለው ከአገር የተባረሩ፣ በአገራቸው ጉዳያቸው በፍርድ እየታየ ካሉ፣ ወደማይቀረው ሞት የተሸጋገሩ ወይም ተቋቁመው እስካሁን በሥልጠናቸው ካሉ መሪዎች ጋር ስናነጻጽራቸው የከፋ በደል የፈጸሙ  ሆነው እናያቸዋለን።

እነዚህ መሪዎች የምዕራባዊያን ወዳጆች በመሆናቸው ምክንያት ብቻ በአገራቸው ምዕራባዊያን የሚዘምሩለት “ዴሞክራሲ” እንደሌለ እየታወቀ የሥልጣን ጊዜያቸውን ለማራዘም የተለያዩ ድጋፎች ሲደረጉላቸው ማየት የዴሞክራሲ መሥፈርቱ ምንድነው? ያስብላል።

የቀለም አብዮቶች በአብዛኛው የሚካሄዱት ምርጫን በመከተል ጎዳና ላይ በሚደረግ ነውጥ በህዝብ ይሁንታ የተመረጡ መሪዎችና የተቋቋመን መንግሥት በሦስተኛ አካል ጣልቃ ገብነት ከሥልጣን

ለማውረድ የሚደረግ ሂደት ነው።  የቀለም አብዮቶች ቀዳሚ ተሳታፊ የሚሆኑት በሠላማዊ መንገድ የተደራጁ ተቃዋሚዎች በተለያዩ መንገዶች በውጭ ኃይሎች በመታገዝ
ሲሆን  በህጋዊ መንገድ ሥልጣን የያዘን መንግስት በተለያየ መንገድ በመወንጀል  **"እምባገነን"** በሚል ፍረጃ ወይም የምርጫ ተከትሎ ሂደቱ ተጭበርብሯል በሚል ሰበብ ብጥብጥ በማስነሳት የግል ፍላጎታቸውን ለማሳካት ሲሯሯጡ ይታያሉ። በዚህ የነውጥ መንገድ  በሰርቢያ በተካሄደው የቀለም አብዮት ስሎቦዳን ሚሎልቭችን ከሥልጣን በማውረድ የመጀመሪያው የተሳካ የቀለም አብዮት ተደርጎ ተወስዷል።
የቀለም አብዮት  ጋር በተያያዘ ብዙውን ጊዜ ስማቸው በተደጋጋሚ ከሚነሱት ግለሰቦችና ድርጅቶች መካከል በዋነኝነት የሚጠቀሱት  ጆርጅ ሦሮውና  በምዕራባዊያን መንግሥታት የሚደገፉ በልማት ስም የሚንቀሳቀሱ የእርዳታ ተቋማት ናቸው። እነዚህ የቀለም አብዮት ደጋፊዎች በህዝብ የተመረጠው መንግሥት ለምዕራባውያን አቀንቃኝ በተለይ አክራሪ የነፃ ገበያ ሥርዓትን የማይከተል መስሎ ከታያቸው እንዲወገድ የተለያዩ መሰሪ አካሄዶችን መተግበር ይጀምራሉ።
እነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች  አገር በቀል የሆኑ የልማትና  የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ነን የሚሉት ድርጅቶችን  በማደራጀት፣ የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ህጋዊ መንግሥታትን በህገ-ወጥ መንገድ ለመገልበጥ ይጠቀሙባቸዋል።
ለአብነትም ኦትፖራ (Otpor) የተባለው አክቲቪስት ግሩፕ በሰርቢያ እንዲሁም ፖራ (Pora) ደግሞ በዩክሬን ለሚያደርጉት የቀለም አብዮት በዩናይትድ ስቴትስ መሠረቱን ካደረገው አልበርት ኢንስታይን ኢንስቲትዩት የስትራቴጂ ሥልጠናና የህትመት ልገሳ ይደረግላቸው እንደነበር ተጠቅሷል። የቀለም አብዮቶች ሁሌም አንድን የህብረተሰብ ክፍል በተለይ በቀላሉ ስሜታዊ ሊሆኑ የሚችሉትን ወጣቶች ለአመፅ መነሳሻነት ይጠቀሙባቸዋል።
የቀለም አብዮት ለማካሄድ የመጀመሪያው ሥራ የአገሪቱን የዴሞክራሲ ተቋማት የሆኑትን ያለምንም ተጨባጭ መረጃ ማቆሚያ በሌለው ውንጀላዎች ደግሞ ደጋግሞ የማጣጣል ሥራ ያለመሰልቸት ይሰራል። በአብዛኛው በዘመቻ ውንጀላ የሚደረግባቸው ተቋማት የምርጫ ቦርድ፣ በየደረጃው ያሉ የፖሊስ ተቋማት፣ የአገሪቱ የፍትህ ሥርዓት፣ ህግ አውጪው አካል ወዘተ ናቸው። እነዚህ ተቋማት ላይ ውንጀላው እጅግ ይበርታ እንጂ ሌሎች የመንግሥት ተቋማትም የስም ማጥፋት ዘመቻው የሚቀርላቸው አይደለም። ከላይ የተጠቀሱት የመንግሥት ተቋማት ላይ ውንጀላውና ስም ማጥፋት ዘመቻው በተከታታይነት የሚሰራው ህብረተሰቡ በእነዚህ ተቋማት ላይ አመኔታ እንዲያጣ ለማድረግ በጥናት የሚከናወን ነው። በአብዛኛው የቀለም አብዮት አራማጆች በምርጫ ተወዳድረው የህዝብን ቀልብ መግዛት የሚያስችል

የፖለቲካ ቁመናም ሆነ ፖሊሲና ስትራቴጂ የሌላቸው በመሆናቸው አቋራጭ የነውጥ መንገዶችን በመጠቀም ወደሥልጣን ለመውጣት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም።

ለቀለም አብዮት ተመራጭ ወቅት በአብዛኛው የምርጫን ተከትሎ እንደመሆኑ ነውጥ ፈላጊዎች ከምርጫ ሂደት በፊትና በምርጫ ወቅት የዴሞክራሲ ተቋማት ላይ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ ይከፍታሉ። የቀለም አብዮተኞች ከምርጫ ወቅት ቀደም ብለው አበክረው የሚሰሩት ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ እንዳልሆነ፣ ምርጫውን ለመምራት የአቅም ማነስ እንደሚታይበት ወዘተ በመንዛት በህብረተሰቡ ዘንድ የተሳሳተ ግምት ለመፍጠር ጥረት ያደርጋሉ።

የቀለም አብዮተኞች በምርጫ ለይስሙላ ይሳተፋሉ እንጂ ምርጫን በአሸናፊነት መውጣት የሚያስችላቸው ፖለቲካዊ ስብዕና የሌላቸው በመሆኑ ትናንሽ ቅሬታዎችን በመሰብሰብ አጀንዳ ለመፍጠር ሲሯሯጡ ይታያሉ። እንዲህ ያሉ ፓርቲዎች ሽንፈታቸውን ቀድመው ስለሚያውቁት በቅድመ ምርጫ፣ በምርጫ ወቅት ወይም በድህረ ምርጫ ወቅት የተለያዩ ምክንያቶችን በመደርደር የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል፣ ድምጻችን ተሰረቀ፣ የምርጫ ሂደቱ ተጭበርብሯል በማለት ድክመታቸውን በእነዚህ ነገሮች ለመሸፋፈን ሲሯሯጡ ይታያሉ።

የቀለም አብዮት ናፋቂዎች የህዝብን ቀልብ ሊስብ የሚችል ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም የጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ ስብዕና የላቸውም። በመሆኑም ገዥውን ፓርቲ በፖሊሲና ስትራቴጂ ከመሞገት ይልቅ በትናንሽና መናኛ ጉዳዮችን በማጎን መንግሥትን በመወንጀል ሥራ ሲጠመዱ ይታያሉ፡፡ ዛሬ በዓለማችን ገንኖ የሚታየው የቀለም አብዮት አነሳስ ይህን ይመስላል፡፡ በቀጣይ በአገራችን ብልጭ ብለው ድርግም ያሉ የቀለም አብዮት እንጭጭ ሙከራዎችን አነሳስና አጠፋፍ፤ የተዋንያኑ ማንነትና ድብቅ አጀንዳዎች ለመዳሰስ ይሞከራል፡፡